ምስጢረ ሥላሴ

በጸጋዬ ክፍሉ

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

አዕማደ ምሥጢር

- **ምሥጢር፡-** ቃሉ የግሪክ ሲሆን ትርጉሙም ደብቅ፣ ሸሽግ፣ ስውር፣ለልብ ወዳጅ ካልሆነ በስተቀር የማይነገር ማለት ነው።
- ቅድስት ቤተክርስትያናችንም ከኢ-አማንያን የምትሸሽገው የምትሰውረው ለአማንያን ብቻ የምተገልጸው የምትፈጽመው ሥርዓት ምሥጢር ይባላል።
- ከሆነ፣ከተከናወነ፣ ከተገለጠ በሁዋላ የሚታወቅ ነገር ምሥጢር ይባላል። የሰማይ አፈጣጠር፣የቃና ወይን
- "ዳግመኛ ልትወለዱ ያሰፈልጋችኋል ስላልሁህ አታድንቅ ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል ድመፁንም ትሰማለህ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንደሚሔድ አታውቅም። ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው" እንዳለ /ዮሐ. 3፡6-8/
- እነዚህን ምሥጢራት ተምሮ ሙሉ በሙሉ ማወቅ አይቻልም

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

- ምሥጢር በሁለት ይከፈላል፤እነሱም
- 1) ገዜያዊ ና ዘላለማዊ
- 2) የፈጣሪና የፈጣሪ

አዕማድ....

- ማለት ዋና፣ምሶሶ፣ቋሚ ማለት ነው።
- ለምን ቢሉ ቤት ያለ ምሶሶ እንድማይቆም ሀይማኖትም ያለ አዕማደ ምሥጢራት አይጸናምና
- መክፈያ ወይም መለያ ማለት ነው፤ያላመኑትን ካመኑት ይለያልና
- የሀይማኖታችን ዶግማ አምስቱ አዕማድ ምሥጢራት ናቸውና
- ለክርስትና እምነት ዋና፣ምሶሶ መሆናቸው ነው።
- ለአምስቱ አእማደ ምሥጢራት ስያሜ መሰረት 318ቱ ሊቃውንት በኒቂያ ጉባኤ ካስታወቁት ከሃይማኖት ቀኖና /ጸሎተ ሃይማኖት/ የተገኘ ነው።

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

አዕማደ ምሥጢር ምሳሌዎች

- የዳዊት 5 ጠጠሮች
- አምስቱ ህብስትና ሁለት አሳ
- 1ኛ ቆሮ 4፤19"አምስት ቃላት በአዕምሮዬ ልናገር እወዳለው"

<u>አዕማደ ምሥጢር</u> - አዕማድ ቤተ ልቡናን በአሚን ያጸናሉ

- አዕማድ ቤተ ልቡናን ከኑፋቄ ይጠብቃሉ
- አዕማድን ያልተማረ ያላወቀ በመንጸፈ ደይን ይወድቃል በእግረ አጋንንት ይረገጣል

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

እነሱም እንደ አቀማመጣቸው ቅደም ተከተል የሚከተሉት ናቸው፡-

- ምሥጢረ ሥላሴ /mystery of the Trinity /
- ምሥጢረ ሥጋዌ /mystery of Incarnation /
- ምሥጢረ ጥምቀት /mystery of Baptism/
- ምሥጢረ ቁርባን / mystery of Holy Communion /
- ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን /mystery of the Resurrection of the Dead / ናቸው።

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire


ሀ. ምሥጢረ ሥላሴን

ለ. ምስጢረ ሥጋዌን

ሐ. ምሥጢረ ጥምቀትን

መ. ምሥጢረ ቁርባንን

ሠ. ምሥጢረ ትንሳኤ ሙታን -



https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

ምሥጢረ ሥላሴ

1 ትርጉም

ሥላሴ የሚለው ቃል ሠለሰ ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ሦስትነት ማለት ነው።

በአጻጻፍ ሥርአት ሲጻፍ **ሥላሴ** ተብሎ ይጻፋል

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

የተሳሳቱ አጠራሮች

➢1 ሦስቱ ሥላሴ

ሥላሴ የሚለው ስም በራሱ ሦስትነት ማለት ስለሆነ ምንም ዓይነት የቁጥር ገላጭ አያስፈልገውም

አንድ ሲሆኑ ሦስት ሦስት ሲሆኑ አንድ ናቸው ከመከፈል ከመቆጠር ውጪ ናቸው

ቅ.ባስልዮስ

➢2 አጋእዝተ ዓለም ሥላሴ

አጋእዝት ማለት ገዢዎች ማለት ነው በገዢነት በሥልጣን ሥላሴ አንድ ናቸው:: ስለዚህ ገዢ እንጂ ገዢዎች አይደሉም

አምላክ እንጂ አማልክት አይደሉም፣ ንጉስ እንጂ ነገሥታት አይደሉም

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

•"እርሱስ አንድ አምላክ ነው እንጂ ፫ አማልክት አይደለም፤ አንድ ጌታ ነው እንጅ ጌቶች አይደለም:: ከፍ ያለ የአምላክነት ክብርም ለመለኮት ነው፤ መግዛትም በመለኮት ነው:: (፳፫ኛ እመልዕክተ ሲኖዲቆን)

•"ከእኔ በቀር ሌላ ባዕድ አምላክ አታምልክ" አለ:: ዘጸ. ፳:፫፤

ዳዊትም:- "ለባዕድ አምላክ አትስገድ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝና ከግብጽ ምድር ያወጣውህ አለ እግዚአብሔር" ብሏል:: መዝ.፹፩፥፱

አንድ አድርጎ በአንድ አንቀጽ “እኔ አምላክህ ነኝ" አለ እንጅ፤

ከሦስት ከፍሎ አብዝቶ “እኛ አማልክትህ ነን" አላለም፤

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

- ሥላሴ በሁለቱም የጸታ አንቀጽ ይጠራሉ

በወንድ አንቀጽ ፡-ሥሉስ ቅዱስ

በሴት አንቀጽ ፡- ቅድስት ሥላሴ

በሴት አንቀጽ መጠራታቸው

1 ስለቸርነታቸው

2 እንግዳ ፍጥረትን በማስገኘት

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

ምሥጢረ ሥላሴ በብሉይ ኪዳን

ምሥጢረ ሥላሴ በብሉይ የነበረ ምሥጢር ቢሆንም በአደባባይ አይሰበክም ነበር

ምሥጢረ ሥላሴ በብሉይ ገሃድ አልነበረም

ለምን አልተነገረም ቢሉ ቅዱስ ጎርጎርዮስ እንዲህ ይላል

1 የሰው ልጅ ጸጋ ተገፎ ስለነበረ መረዳት የሚችልበት አቅም ስላልነበረው

2 አይሁድ መከፋፈል ይወዱ ስለነበር

3 አይሁደ ብዙ አማልክት በላቸው በአህዛብ ይቀኑ ነበርና

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

- ዘፍ 2÷18 “እግዚአብሔር አምላክ አለ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸው ረዳት እንፍጠርለት”
- ዘፍ 3÷22 “እግዚአብሔር አምላክ አለ እነሆ አዳም መልካሙንና ክፉውን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ” እዚህ ላይ እግዚአብሔር አምላክ አለ።
- ዘፍ 18÷1 እዚህ ጥቅስ ውስጥ አብርሃም ሥላሴን በእንግድነት እንደተቀበለ እንመለከታለን። “አቤቱ በፊትህስ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ”
- በማለት እንድነታቸውን ጥቂት ውሃ ይምጣላችሁ እግራችሁን ታጠቡ ማለቱ ሥስትነታቸውን ሲያስረዳ ሚስቱን ሦስት መስፈሪያ የተሰለቀ
- ዱቄት ፈጥነሽ አዘጋጂ ለውሽውም እንጎቻም አድርጊ ማለቱ አንድም ሦስትም መሆናቸውን ያመለክታል።
- ኢሳ 6÷1-3 “አንዱ ለአንዱ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር...”

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

አንድነት	ሦስትነት
"እግዚአብሔር... ተገለጠለት"	"... እነሆ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ"
"... ተነስቶ ወደ ምድር ሰገደ.. አቤቱ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ ባሪያህን አትለፈኝ ብዬ እለምንሃለሁ"	“ጥቂት ውኃ ይምጣላችሁ እግራችሁን ታጠቡ ከዚህችም ዛፍ በታች እረፉ..."
" ለውሺውም እንጎቻም አድርጊ..."	" ሦስት መስፈሪያ የተሰለቀ ዱቄት ፈጥነሽ አዘጋጂ"
”እርሱም የዛሬ ዓመት እንደዛሬው ወደ አንተ በእውነት እመለሳለሁ...”	"እነርሱም ሚስትህ ሣራ ወይት ናት አሉት"
"እግዚብሔርም አለ እኔ የማደርገውን ከአብርሃም እሰውራለሁን"	-

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

- ኢሳ 48÷12 “አሁን ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከወኛል” ተላኪ ወልድ እግዚአብሔር ብሎ አብን መንፈስ ቅዱስ ማመልከቱ ነው።
- መዝ 117(118) ÷16 “የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች፣የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችኝ የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች” ሦስት ጊዜ የእግዚአብሔር ቀኝ ማለቱ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን መጥራቱ ነው ቃሉ አለመለወጡ አንድነቱን ያመለክታል።
- ዘጉ 6÷24 “... እግዚአብሔር ይባርክህ ይጠምቅህም፣እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ ይራራልህም፣ እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሳ ሠላምን ይስጥህ 3 ጊዜ እግዚአብሔር ብሎ መጥራቱ ሦስትነቱን ቃሉ አለመለወጡ አንድነቱን ያመለክታል”

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

የሥላሴ ትምህርት በሐዲስ ኪዳን

- ማቴ 3÷16 “ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ ወድያው ከውሃ ወጣ እነሆም ሠማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ ቅዱስ ርግብ ሲወርድ የእርሱ ላይ ሲመጣ ታየ እነሆም ድምጽ
- ከሠማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይሄ ነው አለ”
- ሉቃ 1÷35 “መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል የልዑል ኃይልም ይጸልልብሻል ስለዚህም ደግሞ ካንቺ የሚወለደው የእግዚአብሔር ልጅ ነው።።”
- 2ኛ ቆሮ 13÷14 “የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔር ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ አንድነት ከሁላችን ጋር ይሁን”
- 1ኛ ዮሐ 5÷7 “በሠማይ የሚመሰክሩት ሦስት ናቸው አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስም ናቸው እነዚህ ሦስቱ አንድ ናቸው”
- ራዕ 14÷1 “አየሁም እነሆ በጉ በጽዮን ተራራ ቆሞ ነበር ከእነርሱ ጋርም ስሙና የአባቱ ስም የመንፈስ ቅዱስም ስም በግንባራቸው ላይ የተጻፈላቸው 144 ሺህ ነበሩ።።”

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

የቅዱሳን አበው ምሥክርነት

- አግናጢዎስ፡- “አብ ወልድን መንፈስ ቅዱስን ወደ መሆን አይለወጥም ወልድም አብን መንፈስ ቅዱስን ወደ መሆን አይለወጥም መንፈስ ቅዱስም አብን ወልድን ወደ መሆን አይለወጥም።እኒህ ሦስቱ አካላት በጌትነት በክብር ፍጹማን ናቸው። በአንድ መለኮት አንድነት አንድ ናቸው” ሃይማኖተ አበው ዘአግናጤዎስ ገጽ 18

ሠልስቱ ምዕት፡- “አብ ወልድ ነው መንፈስ ቅዱስም ነው። ወልድም አብም ነው መንፈስ ቅዱስም ነው። መንፈስ ቅዱስም አብም ነው ወልድም ነው ብለው የሥላሴን አካል አንድ ነው ስም ግን ሦስት ነው የሚሉ የነሰባልዮስ የረከሰች ሃይማኖት እናወግዛለን እንጂ አንድ አካል ሦስት ስም የሚሉ እነዚህ ከእኛ የተለዩ ከሃይማኖታችን የወጡ ናቸው”

ቅዱስ አትናቴዎስ፡-“በባሕሪ አንድ እንደሆኑ በሦስቱ እናምናለን እነዚህም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ናቸው አብ የሚያድን ነው ወልድም የሚያድን ነው መንፈስ ቅዱስም የሚያድን ነው። አንድ ሲሆኑ ሦስት ናቸው ሦስት ሲሆኑ በባሕሪ፣በመለኮት፣በክብር በመመስገን በሥልጣን፣በፍጡራን ሁሉ በመፍጠር፣በፍቃድ፣ኃጢአትን ሁሉ ይቅር በማለት በማትለወጥ እውቀት በረከትን በመስጠት አንድ ናቸው” ሃይማኖተ አበው ገጽ 85

https://www.youtube.com/@tsegayezedire
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

ሥላሴ ስንት ናቸው

- ቅዱስ አትናቴዎስ

አንድ ሲሆኑ ሦስት ሦስት ሲሆኑ አንድ ናቸው

- ቅዱስ ባስልዮስ

አንድ ሲሆኑ ሦስት ሦስት ሲሆኑ አንድ ናቸው ከመከፈል ከመቆጠር ውጪ ናቸው።

- "አንድ እግዚአብሔር አንድ ሕላዌ አንድ መለኮት ብንል፣ አንድ ማለታችን ፫ አካለት ማለትን የሚፈርስብን አይደለም። ሦስት አካለት ማለታችንም መለኮትን ከሦስት የሚከፍልብን አይደለም። ። (ሃይ. አበው፣ እመልዕክተ ሲኖዲቆስ ፶፪ኛ ክፍል ፩)።

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

የሥላሴ አንድነት

ሃይማኖተ አበው ዘአግናጥዮስ

ስለአንድነታቸው ምዕ 01÷6

- በአምላክነት አንድ ናቸው
- በፈቃድ አንድ ናቸው
- በኃይል አንድ ናቸው
- በመንግስት አንድ ናቸው
- በመሰገድ አንድ ናቸው
- በመመስገን አንድ ናቸው
- በምክር አንድ ናቸው
- በሥልጣን አንድ ናቸው
- በክብር አንድ ናቸው
- በሁሉ አድሮ ሁሉን በማክበር አንድ ናቸው

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ ሃይ አበ 4፥6

- ✓በአገዛዝ – መገዛት መታዘዝ የላቸውም አንዱ አንዱን አይገዛውም አያዘውም

  – በጌትነት በክብር አንዱ ከአንዱ አይበልጥም

- ✓በቅድምና - አብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ ዓይን ከፍቶ የሚገጥሙትን ገጥሞ የሚከፍቱትን ያህል አልነበረም

  -ወልድም ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ በዘመን አልነበረም

- •አንድ ልብ፣ አንድ ቃል፣ አንድ ሕይወት፣ አንድ አገዛዝ፣ አንድ ስልጣን፣ አንድ ክብር፣ አንድ አገዛዝ" እንዳለ አባ ሕርያቆስ

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

- በመለኮት:- መለኮት ማለት "መለከ - ገዛ" ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ሆኖ ''ግዛት'' ማለት ነው። በእብራይስጥም ማልኮት ይባላል።
- አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በመለኮት ይህም ማለት በግዛት በመንግስት አንድ ናቸው።
- ''መንግስትህ የዘለዓለም መንግስት ናት ግዛትህም ለልጅ ልጅ ነው::" /144፥13/ /መዝ 145፥10/ /መዝ 73፥12//ዳን 4፡-3/ /ዳን 4፥34/ /1ተሰሎ 2፥12/
- "በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና::" /ቈላስ 2፥9/
- የመለኮቱ ታይል በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰለ ---ሁሉን ሰጠን /2ጴጥ1፥3/
- ''መለኮቱ'' አለ እንጂ ''መለኮቶች'' በማለት አላበዛውም።

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@eotcmezmuredirect

የሥላሴ ልዩ ሦስትነት

መጽሐፈ ኪዳን

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ስንል አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብ እንደ ማለት አይደለም ለእነዚህ ለሦስቱ የስም የአካል ሦስትነት ቢኖራቸውም የባህርይ የዘመን አንድነት የላቸውም

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

1 የአካል ልዩ ሦስትነት

❖ የሥላሴ አካል

1 ያልተፈጠረ አካል

2 ረቂቅ አካል

አፈር → ውሃ → እሳት → ነፋስ → ነፍስ መላእክት

ከእነዚህ ሁሉ ግን እግዚአብሔር ይረቃል

3 በሁሉ የሞላ አካል

የዓለማት ዓለማቸው እግዚአብሔር ነው

ቅዱስ ጎርጎርዮስ

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

የአካል ሦስትነታቸው

ለአብ ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክዕ ፍጹም አካል አለው

ለወልድ ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክዕ ፍጹም አካል አለው

ለመንፈስ ቅዱስ ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክዕ ፍጹም አካል አለው

በአካል አይተባበሩም

በአካል አይበላለጡም

በአካል አይቀዳደሙም

ማስረጃ

1 ዘፍ 18፡-1

2 ማቴ 3፡-16

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

2 የአካል ግብር

ግብር በሁለት ይከፈላል።

1.ባህሪያዊ {ስልጣናዊ}ና

2.አካላዊ

ስልጣናዊ ስንል መፍጠር፣ መስጠት፣ ማዳን...የመሳሰሉት ናቸው ። በስልጣናዊ ግብር ሥላሴ አንድ ናቸዉ።

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

ሃይ.አበው ዘኪራኮስ ምዕ (1*3

በሥራ ፈቃድ አንድ ናቸው፡-

- አብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ በብቻው ሥራውን የሚሠራ አይደለም
  - ወልድም ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ የሚሠራ አይደለም
  - መንፈስ ቅዱስም ከአብ ከወልድ ተለይቶ ሥራውን የሚሠራ አይደለም አብ የሚሠራውን ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይሠሩታል እንጂ

ሦስትነታቸው በአካል ግብር ነው

1 የአብ የአካሉ ግብር መውለድ እና ማስረጽ ነው

2 የወልድ የአካሉ ግብር መወለድ

3 የመንፈስ ቅዱስ የአካል ግብር መስረጽ ነው

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

- የአብ ግብሩ መውለድ የወልድ ግብሩ መወለድ ነው

ስለዚህ አብ አባት ነው ወልድ ልጅ ነው

(ዮሐ.15:23) እኔን የጠላ አባቴንም ይጠላል።

(ሉቃ.9.28-36)"እነሆምከደመናው በእርሱ ደስ የሚለኝ ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት።“

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

ወልድ ተወለደ ሲባል

አባቱ ፡-1 በዘመን ሳይቀድመው

“ሰው አባት ሲባል ከልጁ እንዲበልጥ ነገሩ የታወቀ ነው:: አባት መባሉም ከልጁ አስቀድሞ እንደነበረ ያስረዳል'' :: ለወልድ እና ፤አብ ግን፣ መቅደም መቀዳደም መብለጥ መበላለጥ የለበትም::

ቅዱስ ቴዎዶጦስ ዘእንቆራ

“ማንም ማን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ መካከል ሊገባ አይችልም:: አኗኗሩ እንደምንም እንደሆነ ያውቅ ዘንድ፣ አብ ልጁን ወልዶታል:: ነገር ግን አብ ልጁን በዚህ ጊዜ እንዲህም ባለ ዘመን ወለደው አይባልም፤ ከአብ መወለዱ አይመረመርም፣ የሚያስጨንቅ ነውና፤ አኗኗሩ አይታወቅም የተሰወረ ነውና፤

“በመለኮት ባሕርይ ይህን ማሰብ ለእኛ አይገባንም፣ ወልድ ዋሕድ በዘመን ሁሉ ከአብ ጋር የነበረ ቀዳማዊ እንደሆነ እናምናለን እንጂ

ሃይማኖተ አበው

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

2 በአካል ሳይቀድመው

ሦስት ነገሮች ያስደንቁኛል

አባቱ የማይቀድመው ልጅ

እናቱን የፈጠረ ልጅ

የፈጠራትን የወለደች እናት

አባ ገዮርጊስ ዘጋስጫ

3 ወለደው እንጂ አልፈጠረውም

የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ

ሠለስቱ ምዕት

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

❖ **የአብ ግብሩ ማስረጽ ነው የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ መስረጽ ነው**

(ዮሐ.15:26) **ነገር ግን ከአብ የሚወጣና እኔም ከአብ የምልከላችሁ የእውነት መንፈስ፣ አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ፣ ስለኔ የመሰክራል።**

➢ **መንፈስ ቅዱስ የሰረጸው ከአብ ብቻ ነው ካቶሊኮች ከወልድም ይላሉ ሰራጺነትን እና ተፈናዊነትን ያምታታሉ**

ከአብ የሚወጣና

ሰራጺነት

እኔም ከአብ የምልከላችሁ

ተፈናዊነት

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

መንፈስ ቅዱስ ማነው?

- መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ሳይሆን ከአብ ብቻ የሰረጸ /የወጣ/ "... ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ" እንዲል /ዮሐ.15፡26/።
- **ሀ. መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው**
- "በእግዘአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ" ሲል የመንፈስ ቅዱስን እግዚአብሔርነት (ፈጣሪነት) ያስረዳል /መዝ32፡6/
- "በሁሉ በምልዐት የሚኖር ይህ መንፈስ ቅዱስ ነው። በሚያምንበት <u>በአንዱም በአንዱም</u> ሁሉ ላይ እርሱ ኩለንተናው (ፍጹም አካሉ) አድሮ ይኖራል እርሱ ሁለንተናው በእግዚአብሔር አብ በእግዚአብሔር ወልድ ህልው ነው እስትንፋሳቸው ነውና" (ሃ.አበው ዘባስልዮስ ምዕ 33 ቁጥር 57)

ለ.መንፈስ ቅዱስ አካለዊ (አካል ያለው) ነው

- "ሐዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም /In The Name of the Father, and of the Son, and of the Holy Ghost /እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው"
- "እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል" /ዮሐ 16፥13/
- "መንፈስ ቅዱስ በርናባስና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ" /የ.ሐዋ 13፥2/

ሐ.ከሳቴ ምሥጢር (ምሥጢር ገላጭ) ነው

- "በመንፈስ ግን ምስጢርን ይናገራል" እንዲል /1ኛ ቆሮ14÷2/

መ. አጽናኝ (Comforter)ነው

"አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል" ዮሐ(14÷26)

ሠ.ወሃቤ ፀጋ(ፀጋን የሚሰጥ) ነው

መንፈስ ቅዱስ አንድ ቢሆንም ስጦታዎቹ ግን ልዩ ልዩ ናቸው /1ኛ ቆሮ12÷4/

"የእግዚአብሔር መንፈስ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ የምክርና የኃይል መንፈስ የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ...." /ኢሳ 11÷2/

"ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ" /ኤፌ.4÷30/

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

መጠሪያ	ስጦታው	አስረጅ
መንፈስ ቅዱስ	ቅድስና	ሉቃ 4፥1 ዕብ 10፥15
አጽናኝ	መጽናናት (መረጋጋት)	ዮሐ 16፥7 ዮሐ 14፥26
የዕውቀት መንፈስ	እውነት (ሃይማኖት)	ዮሐ 14፥17 15፥26 ዮሐ 16፥13
የተስፋ መንፈስ	በተስፋ መሞላት	የ.ሐዋ 1፥5
የሕይወት መንፈስ	ዘላለማዊ ሕይወት	ዮሐ 6፥63 ሮሜ 8፥2
የቅድስና መንፈስ	ቅድስና (በኑሮሁሉ)	ሮሜ 1፥4
የልጅነት መንፈስ	የጸጋ ልጅነት	ሮሜ 8፥15
የፍቅር መንፈስ	መንፈሳዊ ፍቅር	2ኛ ጢሞ1፥7
የኃይል መንፈስ	መንፈሳዊ ኃይል	2ኛ ጢሞ1፥7
ራስን የመግዛት መንፈስ	ራስን መግዛት	2ኛ ጢሞ1፥7
የጸጋው መንፈስ	አጠቃላይመንፈሳዊ ስጦታዎች	ዕብ 10፥29

4 የስም ሦስትነት

4.1 የአካል ስም ሦስትነት

አብ ፤ወልድ ፤መንፈስ ቅዱስ

4.2 የአካል ግብር ሦስትነት

ወላዲ አስራጺ ፤ ተወላዲ ፤ ሰራጺ

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

የኩነት ሦስትነት

- ኩነት ማለት ‹መሆን› ወይም ‹መባል› ማለት ነው።
- ለምሳሌ ከዊነ ልብ፣ ከዊነ ቃል፣ ከዊነ እስትንፋስ ሲል ልብ መሆን ወይም መባል፣ ቃል መሆን ወይም መባል፣ እስትንፋስ መሆን ወይም መባል ማለት ነው።
- ስለዚህ ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ ሦስቱ አካላት ሥላሴ የሚጠሩበት የኩነት ስም ማለት ነው።

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

- የአብ ኩነት ልብ (ልብነት) ሲሆን በራሱ ለራሱ ልቡና አእምሮ ነው። ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ልቡናቸው (ማወቂያቸው) ነው፤ ከእርሱ ሌላ ልቡና የላቸውም።
- የወልድ ኩነት ቃል (ቃልነት) ሲሆን በራሱ ለራሱ ቃል ነው። ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው (መናገሪያቸው) ነው። ከእርሱ ሌላ ቃል የላቸውም።
- የመንፈስ ቅዱስ ኩነት እስትንፋስ (ሕይወትነት) ሲሆን በራሱ ለራሱ ሕይወት ነው። ለአብና ለወልድ እስትንፋሳቸው (ሕይወታቸው) ነው። ከእርሱ ሌላ ሕይወት የላቸውም።

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

ኩነታት በመጽሐፍ ቅዱስ

•**የአብ ኩነት ልብነት ስለመሆኑ** ‹‹የእግዚአብሔር ምክር ግን ለዘለዓለም ይኖራል፤ የልቡም (የአብ) አሳብ ለልጅ ልጅ ነው›› መዝ፡-32፥11 በማለት የአብ ኩነት ልብነት (አዋቂነት) እንደሆነ ተገልጿል።

•**የወልድ ኩነት ቃል ስለመሆኑ** ደግሞ ‹‹በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ›› መዝ፡-32፥6 ‹‹ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ›› ዮሐ፡-1፥14 ‹‹ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ ...›› ዕብ፡-11፥3 በማለት የእግዚአብሔር ወልድ ኩነት ቃል መሆኑን መመልከት እንችላለን። ቅዱስ ዮሐንስም በራእዩ የወልድን ኩነት ስሙ ቃል እንደሆነ እንዲህ ሲል ገልጾታል፡- ‹‹ ... ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሏል›› ራእ፡-19፥13 ብሎ ገልጾታል።

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

- **የመንፈስ ቅዱስ ኩነት እስትንፋስነት መሆኑን** በተመለከተ ክቡር ዳዊት ‹‹በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፤ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ›› መዝ፡- 32(33)፥6 ብሎ ተናግሮአል። ኢዮብም ‹‹እርሱ ልቡን ወደ ራሱ ቢመልስ፣ መንፈሱንና እስትንፋሱን ወደ ራሱ ቢሰበስብ፤ ሥጋ ለባሽ ሁሉ በአንድነት ይጠፋል›› ኢዮ፡-34፥14 በማለት የመንፈስ ቅዱስ ከዊን እስትንፋስነት (ሕይወት) ተናገረ።

- የስም ተመሳሳይነት፡- የነፍስ ኩነታት (ጠባይዓት) ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ ይባላሉ።

  የሥላሴም ኩነታት ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ ተብለው ይጠራሉ።

- ነፍስ በአካልዋ አንድ ስትሆን በኩነት ግን ሦስት ናት። በዚህም ለሥላሴ አንድነት እና

  ሦስትነት ምሳሌ ትሆናለች።

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

የፍጡራን ምሳሌ

ቅዳሴማርያም 5*&1-&5

1 ጸሐይ

- አንድ ስትሆን ሦስት ኩነት አላት

  አካል--የአብ

  ብርሃን-የወልድ

  ሙቀት-የመንፈስ ቅዱስ

- እነዚህ ሦስቱ አይቀዳደሙም
- ብርሃንም ሙቀትም ከአካል ይገኛሉ

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

በምሥጢረ ሥላሴ ዙሪያ የተነገሩ የስህተት ትምህርቶች

1 አርዮስ

- ሦስት ጊዜ የተወገዘ መናፍቅ ነው
- ለብዙ ዘመን የቤተክርስቲያን ችግር ምክንያት ነበር
- ከክፉ ሥራው አልመለስ በማለቱ ተቀስፎ ሞተ

የአርዮስ የስህተት ትምህርቶች

1 መአረገ መንግስት መስጠት

አብ >ወልድ > መንፈስ

2 ወልድ ፍጡር ነው

- መወለድ እና መፈጠር ሞክሼ ቃላት ናቸው
- አብ ፍጥረትን ከመፍጠሩ በፊት በመጀመሪያ ወልድን ፈጠረ

https://www.youtube.com/@mezmuretewahido1tube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

የቅዱስ አትናቴዎስ መልሶች

1 የሥላሴ መንግስት የማትከፈል የማትበላለጥ አንዲት መንግስት ናት

እኔና አብ እንድ ነን አለ ዩሐ ፲፯÷፳፪

እኔ ያየ አብን አየ አኔና አብ አንድ ነን ዮሐ.፲፬

2 ወልድ ፍጡር አለመሆን

- መወለድ እና መፈጠር ሞክሼ ቃላት አይደሉም አብ በሰጠው ምስክርነት ልጄ አለው እንጂ ፍጥረቴ አላለውም
- መጽሐፍ የመጀመሪያ ፍጥረት ሰማይና ምድርን እንጂ ወልድን አይልም
- አብ ፍጥረትን ለመፍጠር የወልድ መሣሪያነት የሚያስፈልገው ከሆነ ወልድን በምን መሣሪያነት ፈጠረው
- ወልድ ፍጡር ከሆነ የሰው ልጅ አልዳነም ማለት ነው

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

3 በባህርይው ከአብ ጋር አንድ የሆነ

ጉባኤ ኒቂያ

1 ኦርቶዶክሳዊያን አባቶች፥-318 ሊቃውንት

በባህሪው ከአብ ጋር አንድ የሆነ

2 አርዮሳዊያን ፥-በአርዮስ የሚመሩ መናፍቃን

መአረገ መንግስት የሰጣሉ

3 ተረፈ አርዮሳዊያን ፥-በአውሳቢዮስ ዘኒቆዲሚያ የሚመሩ

ከአብ ጋር የተካከለ ነው

ሥላሴ በስልጣን

በአገዛዝ አንድ ናቸው

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

ኩነታት(መሆኖች)

- "በእግዘአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ" /መዝ32፡6/
- በአብ ልብነት ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሕልዋን ናቸው ስለዚህም በአብ ልብነት ያስባሉ፤
- በወልድ ቃልነት አብ መንፈስ ቅዱስ ሕልዋን ናቸው ስለዚህ በወልድ ቃልንት ይናገራሉ፤
- በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት አብ ወልድ ሕልዋን ናቸው ስለዚህ በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት ህያዋን ሆነው ይኖራሉ፤

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

መከፋፈል የሌለባቸው ሦስቱ ኩነታት

ከዊነ ልብ (ልብ መሆን)	በአብ መሠረትነት ለራሱ ለባዊ (አሳቢ) ሆኖ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ዕውቀት ማወቂያ መሆን ነው
ከዊነ ቃል (ቃል መሆን)	በአብ መሠረትነት ለራሱ ነባቢ(ተናጋሪ) ሆኖ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ንባብ (መናገሪያ) መሆን ነው
ከዊነ እስትንፋስ (እስትንፋስ መሆን)	በአብ መሠረትነት ለራሱ ሕያው ሆኖ ለአብና ለወልድ ሕይወት መሆን ነው

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire

በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት ሊጠኑና ሊያዙ የሚገባቸው ዋና ዋና ነጥቦች ናቸው ሰንጠረዥ.2

አንድነት	ሦስትነት
ባሕይር	ስም
መለኮት	አካል
ህልውና	ግብር
አገዛዝ	ኩነታት(መሆኖች)
እግዚአብሔርነት	
አኗኗር	

https://www.youtube.com/@mezmuretewahidotube
/videos www.tiktok.com/@tsegayezedire